**የጨረታ ቁጥር፡- አባ/ግክ/103/2024**

# የመጋዘን ኪራይ አገልግሎት ግዢ ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

አማራ ባንክ አ.ማ ለመጋዘን አገልግሎት የሚውልና ለዚሁ ዓላማ የተገነባ እና በቂ ግቢ ያለው ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን መከራየት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መጋዘኖች ያሏችሁና ለማከራየት ፍላጐት ያላችሁ ባለንብረቶች ወይም ተወዳዳሪዎች በዚህ ጨረታ እንድትሳተፉ ይጋብዛል፡፡

ሀ/ ህንፃው የሚገኝበት አካባቢ (location)

- ቂርቆስ እና አካባቢው
- ን/ላፍቶ እና
- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አመቺ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኝ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ/ ህጋዊ መስፈርቶች

- የመጋዘኑ ህጋዊ ባለቤትና ይዞታ፣ ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም ፍቃድ ማቅረብ የሚችሉ፣
- መጋዘኑ የሚከራይበት ወርሃዊ ዋጋ በማካተት በሰም በታሸገ ኤንቨሎኘ ማቅረብ የሚችሉ፣
- የመጋዘኑ ህጋዊ ይዞታነት በከተማው ማስተር ፕላን የተደገፈ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርበታል፡፡

ማሳሰቢያ፣

1. ተጫራቾች ዝርዝር የጨረታ ሠነዱን ከለገሃር ወደ አዲስ አበባ ስታዲየም በሚወስደው መንገድ መብራቱን እንደተሻገሩ የአመልድ ህንፃ ላይ በሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ግዢና ፋሲሊቲዎች መምሪያ 20ኛ ፎቅ ላይ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር ብቻ / በህንፃው ምድር ወለል ላይ በሚገኘው አዲስ አበባ ቅርንጫፍ በመክፈል ማግኘት ይችላሉ፡፡
2. **የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ጊዜ እስከ ነሐሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ 7:30 ድረስ** ብቻ ነው፡፡
3. ጨረታው **ነሐሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ በ8:00 ሰዓት ባለንብረቶች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ ይከፈታል፡፡**
4. በውድድሩ ወቅት ባለንብረቶች ሁሉንም ህጋዊ ሰነዶች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ባንኩ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ**

- *ለገሀር አካባቢ በሚገኘው የአማራ ባንክ አ.ማ ዋና መ/ቤት 20ኛ ፎቅ በግዢና ፋሲሊትስ ማኔጅመንት መምሪያ በአካል በመቅረብ ወይንም በስልክ ቁጥር 0115582905 ወይም 0115584491 በመደወል መረጃ መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡*

***አማራ ባንክ አ.ማ***